# ተረት ተረት -

# ሌባ ወይስ ሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት

መላኩ ከአትላንታ

**05/02//2018**

ሰሞኑን በጣም አስቂኝ የሆነ ተረት  እያደመጥን ነው።ተረቱን በጣም አስገራሚ ያደረገው ደግሞ ይህ አስቂኝ ነገር እየመጣ ያለው ከገዢው ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች ሳይሆን ፤ተቃዋሚ ነን ከሚሉ ፖለቲከኞችና አቀንቃኞች መሆኑ ነው።ሃገራችን ኢትዮጲያ ባለፉት አርባ አራት አመታት ፤ከሃጴ ሃይለስላሴ ወዲህ ለመጀመርያ ጊዜ እግዚአብሄር ኢትዮጲያን ይባርክ የሚል ፤ፈሪሃ እግዚአብሄር ያለው ፤ ሃገራችንን በክብር ስሟ ኢትዮጲያ ብሎ ከመጥራትም አልፎ ኢትዮጲያ ለዘላለም ትኑር ሲል እየተደመጠ ያለ ፤ በበርካታ ኢትዮጲያውያን አዕምሮ ተስፋን ያጫረ አዲስ መሪ እያስተናገደች ነው።ያም ብቻ ሳይሆን አዲሱ ጠቅላይ ሚ/ር የራሴ ራዕይ አለኝ የሚሉና ለዛም አደርጋለሁ የሚሏቸውን ነገሮች በግልፅ ሲናገሩ እያደመጥን ነው።ከነዚህም አበይት የሚባሉት የደህንነት መስሪያ ቤቱን ሃገራዊ ተዋፅኦ በጠበቀ መልኩ እንደገና ማደራጀት፥የህግ ማሻሻያዎች ማድረግ፤ተፎካካሪ ለሚባሉት የፖለቲካ ድርጅቶች የፖለቲካ ምህዳርን ማስፋት ብቻ ሳይሆን መክፈት ወዘተ ናቸው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ አደርጋለሁ የሚሏቸውን ነገሮች ተግባራዊ ያደርጋሉ አያደርጉም የሚለው ላይ ኢትዮጲያውያን የተለያየ ሃሳብ እየሰጠንና እያደምጥን ነው። የጠቅላይ ሚኒስትሩ ሹመት በህወሃት የተሸረበ ሴራ ወይም ትዕይንት ነው በማለት በጨለምተኝነት ህሳቤ ውስጥ ያሉትን ወደ ጎን ትተን ፤ዶር አብይ የህዝቡ የትግል ውጤት ናቸው ብለን ከምናስበው መንደር እየተደመጠ ያለ አስገራሚና አስቂኝ ተረት "ኢህአዴግ እሰራሩ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ስለሆነ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር ቃል የገቡትን ለመፈፀም አይችሉም ወይም ይህ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚባል አሰራር አይፈቅድላቸውም" እየተባለ የሚነገረው ቧልት ነው።ኢህአዴግ ፤ልብ በሉና ህወሃትን ማለቴ አይደለም ፤ኢህአዴግ አሰራሩ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ነው ብሎ ማሰብና ያንንም እንደገደል ማሚቶ ማስተጋባት ስህተት ብቻ ሳይሆን፤የለውጥ እንቅፋት ለሆነው ዘረኛ አንድ የደቡብ አባት እንዳሉት ሌባ ቡድን ፤ሌላ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚል የማሞካሻ ጭምብልት በማልበስ ለሌቦቹ የመደበቂያ ጉሮኖ በማበጀት የህዝብን የእኩል ተጠቃሚነትና የዲሞክራሲ ጥያቄ ከሚያፍኑ ጋር መተባበር ነው።

ለመሆኑ ዲሞክራሲ ማዕከላዊነት ምንድን ነው ብለን ብንጠይቅ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚለው ቃሉ ሶስት የተለያዩ መሰረተ ሃሳቦችን ያቀፈ ነው ።ይህንንም ሃሳብ ለመጀመርያ ጊዜ ይዞ የመጣው የሩሲያው የቮልሾቪክ ፓርቲ መሪ የነበረው ሌኒን በፓርቲው አስረኛ ኮንግረስ ስብሰባ ማለትም በ 1921 ሲሆን በዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ስር የታዘሉት ሶስት ሃሳቦች የሚከተሉት ናቸው።

i. ኮሚኒስት ፓርቲው የቆመው ለሰራተኛው መደብ ስለሆነ ከዚህ መደብ ጥቅም በተቃራኒ የቆሙ ዘለዓለማዊ ጠላት ስለሆኑ የነዚህን ጠላት ተብለው የተፈረጁ ቡድኖች ሃሳብ አለማስተናገድ ብቻ ሳይሆን ቀጥተኛ አፈና ማካሄድ ።

ii. ወሳኝና የተለያየ አቋም ሊያስይዙ የሚችሉ የአቅጣጫ ውይይቶች በፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት ብቻ የእኩል ዲሞክራሲ ወይም ነፃ ውይይት ባለበት በሙሉ መግባባት እንዲወሰን።እዚህ ላይ በኮሚኒስቶቹ አሰራር የተለየ ሃሳብ ይዞ በድምፅ ተበልጫለሁ የሚባል እካሄድ የለም።ሁሉም እዛው ስብሰባው ውስጥ መስመሩን ማስትካከል ይጠበቅበታል።አለበለዝያ አንጃ ተብሎ ይፈረጃል፤ እርምጃም ይወሰድበታል።

iii. ከላይ እንደተገለፀው በፓርቲው ውስጥ የተለያዩ ሃሳቦች እንዲንሸራሸሩ መፍቀድ አንጃዎችን ስለሚፈጥር ውሳኔዎች በበላይ አካላቱ ዲሞክራሲያዊ ውይይት ይወሰናሉ ከዛ በኋላ የሌሎች የፓርቲ አባላት ሚና ያንን ማዕከላዊ ውሳኔ መረዳትና ማስፈፀም ላይ ብቻ የተወሰነ ነው። ማንም የፓርቲው አባል ከማዕከላዊው ኮሚቴ ውሳኔ ውጪ የሆነ ሃሳብን ማስተናገድ አይችልም ።

በአንፃሩ ምዕራባዊው ዲሞክራሲያዊ ስርዓት በሰፈነበት እንደነ አሜሪካ ግን የፓርቲው አባል ሆኖ ግላዊ ሃሳብን እንደሁኔታው ማንፀባረቅ ይቻላል።ለምሳሌ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ 2004 በአሜሪካን የዲሞክራቲክ ፓርቲ አባል የሆነው ዜል ሚለር የራሱ የዲሞክራቲክ ፓርቲ እጩ የሆነውን ጆን ኬሪን ሳይሆን የተቃራኒ ፓርቲ እጩ የነበረውን ጆርጅ ቡሽ በመደገፍ በሪፐብሊካኖች ስብሰባ ተገኝቶ የራሱን ፓርቲ እጩ ሲቃወም ተመልክተናል።በቅርቡም የሪፐብሊካን አባል ብቻ ሳይሆን በዛም የኒው ዮርክ ከንቲባ እስከመሆን የደረሰው ማይክል ብሉምበርግ የሪፐብሊካን ፓርቲ የፕሬዜዳንትነት እጩ የሆነው ትራምፕን ተቃውሞ የተቃራኒ ፓርቲ እጩ የሆነችውን ሂለሪ ክሊንተን ደግፎ ከዲሞክራቶች ጋር ተባብሯል።የፓርቲ አባል ለመሆን አባል የሆነበትን ፓርቲ ፖሊሲና አካሄድ ሁሉ አይን ጨፍኖ መደገፍን አይጠይቅም።የሀገር ጥቅም ከድርጅት በላይ ተደርጎ ስለሚታይ።በተቃራኒው ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚለው ሃሳብ ስራው እንደዚህ የፓርቲ አባላት የተለያ ሃሳብ ማስተናገድ እንዳይችሉ ለመገደብም የተወጠነ ነው።

እነዚህን መሰረታዊ እውነታዎች ተረድተን መቼና የት በንድፈ ሃሳብም ሆነ በታሪክ ኢህአዴግ የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን አስተናገደ ወይም የዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት አራመደ ብለን እንጠይቅ።

1. ቮልሾቪክ ለሰራተኛው መደብ የቆመ ነበር ፤ኢህአዴግ የቆመው ለማን ነው? ይህ የቂል ጥያቄ ሊመስል ይችላል። ግን በውስጡ የኢትዮጲያ ህዝብ ከዕለት ተዕለት ኑሮው የሚመለከታቸው ብዙ መራራ እውነታዎች እንዳሉ ያሳያል።እያንዳንዳችን ለዚህ ጥያቄ መልስ ለመስጠት በምንሄድበት የሃሳብ መንገድ በርካታ ዘግናኝና አንገሽጋሽ ሁኔታዎችን እንድናስታውስ እንገደዳለን።ባሁን ሰዓት ኢህአዴግ የሚለው ስም እራሱ በርካታ ኢትዮጲያውያንን የሚያስቆጣ ነው።ኢህአዴግ አትበል ህወሃት በል።ኢህአዴግ የሚባል ነገር የለም።ኢህአዴግ የህወሃት ጭንብል ነው ወዘተ ወዘተ የሚሉት ባሁን ሰዓት ገነር ሃሳቦች ናቸው።

ከዶር አብይ በኋላ ያለውን ለጊዜው እንተወውና ሃቁ ኢህአዴግ የቆመው ለህወሃት ሲሆን ህወሃት ደግሞ የቆመው ለትግራይ ህዝብ ሳይሆን አዲስ ለፈጠረው ለራሱ አጥንት ተኮር የሆነ ገዢ መደብ ነው።ቮልሾቪክ ውስጥ አባል ለመሆን የሚያስፈልገው የሰው ልጅ መሆን ነበር አንዱ ካንዱ የሚበልጠው ለራሱ ለሰው ልጅ ጥቅም በሚያራምደው አመለካከት ነው።ኢህአዴግ ውስጥ አራት ድርጅቶች አሉ ።አንድ ሰው ከህወሃት በመምጣቱና ባለመምጣቱ ብቻ ኢህአዴግ ውስጥ ያለው ደረጃ ይለያያል።እውነቱ ይህ ነው።በነዚህ አራት የተለያዩ መንደሮችን እንወክላለን በሚሉ ስብስብ ዲሞክራሲ አይደለም የጋራ አጀንዳም ሊኖር አይችልም። አንቱ መባልና የግል ጥቅምን ማካበት እንጂ።

2. ኢህአዴግ ውስጥ ዲሞክራሲ ነበረ ወይ? ይህ ጥያቄ ማብራሪያ የሚያስፈልገው አይመስልም። መስሱ ግልፅ ነው።ኢህአዴግ በአቶ መለስ ዜናዊ ይታዘዝ የነበረ ድርጅት ነው።የተለየ ሃሳብ አቅርቦ የሚከራከርና የመለስንም ሃሳብ የተቃረነ አማራጭ አቅርቦ የጋራ መስማማት በመፍጠር ማስወሰን የሚችል ድርጅት አልነበረም። ከዚህ የምንረዳው የኢህአዴግ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባላት የሚባሉት ጭምር እንወክለዋለን ያሉትን ህዝብ ጥቅም ለቅርጫ አቅርበው አረቄ ሲጨልጡ የከረሙ፤ እራሳቸው የአስተሳሰብ ባርያዎች ፤በአንፃራዊነት የዲሞክራሲ እጦት ሰለባዎች መሆናቸውን ነው።ወደዱም ጠሉም የሚሰጣቸውን አጀንዳ ቆሻሻም ቢሆን እንዳለ ከማስፈፀም ውጪ ሌላ ምንም ድርሻ የላቸውም።ግን እንደ ተቀዳሚ የስርዓቱ አገልጋይ ተቀዳሚ ተጠቃሚዎች ነበሩ ናቸውም።ይህ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት ከሚለው ቃል ዲሞክራሲያዊ የሚለው ሙሉዉን የተሰረዘ መሆኑን በግልፅ የሚያሳይ አስረጅ ነው።

ትንሽ ነቃ ያለ ሰው ሌኒንስ እራሱ ዲሞክራት ነበረ ወይ ሊል ይችላል። ትልቁ ነገር ሌኒን በጊዜው ያራመደው ሃሳብ ሰፊና አለም አቀፋዊ ከመሆኑ አንፃር በርካታ አባላቶቹ በሌኒን ጥያቄ ስር የመካተትና በዛም ውስጥ የኔ ነው ብለው ዲሞክራሲያዊ ተሳትፎ የማድረጋቸው ዕድል እጅግ ሰፊ ነበር።ስለ ሰው ልጅ ሲወራ ሁላችንን ይጨምራል።ስለ አንድ መንደር ጥቅም ሲወራ ሃሳቡ ብዙዎችን የማግለል እድሉ እጅግ በጣም ሰፊ ነው።ከዛ መንደር ላልመጡ።ሌኒን ያሰበው ማዕከላዊ ኮሚቴ የአለም ሰራተኞችን በሙሉ በእኩልነት ያቀፈ እንጂ አጥንት ተመልክቶ ከፊሉን የፓርቲው የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ቀዳሚ ትዕዛዝ ሰጭ አብዛኛውን የፓርቲ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባልና ተከታዮች ደግሞ ሁለተኛ ወይም ትዕዛዝ ተቀባይ የሚያደርግ አልነበረም።እኩል ጡንቻ በሌላቸው የተለያዩ መንደሮችን እንወክላለን በሚሉ የጋራ ጥቅም በሌላቸው አራት ጎረምሶች መሃከል እንዴት እኩል ዲሞክራሲያዊ ውይይት ይኖራል።

3. ማዕከላዊነት? በትክክል- ኢህአዴግ በማዕከላዊነት አሰራር ይታወቃል።ዲሞክራሲያዊነት የሚለው ግን የለበትም። ለምን? ጠቅላይ ሚንስትሩ ያመጣውን ሃሳብ ሁሉም አሜን ብሎ መቀበል ግዴታው ነው።ያም የደህንነት መስሪያ ቤቱን፤ የመከላከያ ሚንስትሩንና ህወሃትን እራሱን ይጨምራል።ሁሉም ጾጥ እረጭ ብለው ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይታዘዛሉ።ያ አካሄድ የቆመው አቶ ሃይለማርያም ወደ ጠቅላይ ሚንስትርነት ሲመጡ ነው።የዛም መነሻ በሳቸው ላይ ወይም በሳቸው ጊዜ የፓርቲ ዲሞክራሲ ሰፍኖ ፤ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚለው አሰራር ስለተፈለሰፈ ሳይሆን አቶ ሃይለማርያም ሙሉ ስልጣን ባለመረከባቸው ነው።የአቶ ሃይለማርያምን ስልጣን የተቀራመቱ በርካታ ምክትሎችና አማካሪዎች ነበሩ።የሚያሳዝነው ችግሩን ሲያቦኩና ሲጋግሩ የነበሩት ስማቸው ሳይነሳ ፤ፍየል በበላ ዳዋ ተመታ እንዲሉ የመፍትሄው አካል ይሁኑ ተብለው ወይም ለችግሩ ተጠያቂ ሆነው ስልጣን የለቀቁት አቶ ሃይለማርያም ብቻ ናቸው።ሌሎቹ አሁንም ተመልሰው ወደ መድረክ ብቅ ለማለት አድብተው እየጠበቁ ነው።

ኢህአዴግ በተለያዩ ጊዜያት ከአንድ ግለሰብ ወይም ከአንድ ቡድን የሚመጣን አቅጣጫ ራዕይ በማለት ሲያስፈፅም የነበረ ነው።ድርጅቱ ውስጥ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚባል አሰራር አልነበረም።አሁንም የለም። ሰለዚህ አሁን በመጀመርያ መጠየቅ ያለብን ክቡር ዶር አብይ ሙሉ የጠቅላይ ሚኒስትር ስልጣኑን እንዳለ ተረክበዋል ወይስ አልተረከቡም የሚለው ነው። አዲሱ ጠቅላይ ሚንስትር እያቀነቀኑ ያለውን የለውጥና የሃቀኛ ተሃድሶ ሂደት እንዳይተገብሩ እንቅፋት የሚሆኑትን ሃይሎች በትክክለኛ ስማቸው ዘረኞች ሌቦች ብለን ልንጠራቸውና ልናውቃቸው ይገባል።በመለስ ጊዜ ያልነበረ ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነትን አሁን እንደሰበብ ማቅረብ ትልቅ ወንጀል ነው።ሌቦችንና ዘርኞችን ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት በሚል ካባ መሸፈን ተረት ብቻ ሳይሆን አደገኛ አስተሳሰብ ስለሆነ መቆም አለበት።የጠቅላይ ሚንስትሩን ስልጣን በተለያዩ ተረት ተረቶች ለመሸርሸር የሚደረጉ እሳሳች አካሄዶችንና ስብስቦችን ነቅሶ በመለየት ተቃውሞውን በመቀጠል የአቶ አብይን የለውጥ ሂደት እንዲፋጠን ማገዝ ከፍተኛ ጠቀሜታ ይኖረዋል።

ዶር አብይ የብዙ ኢትዮጲያውያን የትግልና የመስዋዕትነት ውጤት ናቸው።እያቀነቀኑ ያለው የለውጥ ሃሳብ መልካም ነው።ለዚህ እንቅፋት የሚሆን በሙሉ ምክንያት ብለን ብንጠይቅ የምናገኘው መልስ ሌብነትና ዘረኝነት ብቻ ነው። ስለዚህ ሌቦችን ሌቦች ዘረኞችን ዘረኞች ብለን በትክክለኛ ስማቸው እንጥራቸው።

ዲሞክራሲያዊ ማዕከላዊነት የሚባ

ተረት ተረት ይቁም!

ኢትዮጲያ በልጆቿ ጥረት ታፍራ ተከብራና በልፅጋ ለዘላለም ትኑር!

መላኩ ከአትላንታ